# የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት)

# ብሔራዊ ም/ቤት የአቋም መግለጫ

በቀድሞው የቅንጅት አመራሮች እና በመንግሥት መካከል ምርጫ 97ትን ተከትሎ በተፈጠረው አለመግባባት በሀገር ሽማግሌዎች አማካኝነት በተመቻቸው የሀገር ባህል የእርቅ ሂደት መሠረት የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት) ሊቀመንበር ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሣ ይቅርታ መጠየቃቸውን ሳይክዱ በመንግሥት የተወሰደባቸውን እርምጃ አስመልክቶ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው የሰጠው መግለጫ በጽሞና በማዳመጥ ም/ቤቱ የሚከተለውን የአቋም መግለጫ አውጥቷል፡፡

የሀገር ሽማግሌዎቹ፤ እስረኞቹ ከእስር በወጡበት እለት በመንግሥት መገናኛ ብዙሃን የገለጹት 18 ወራት ከፈጀ የሽምግልና ጥረት በኋላ እስረኞቹን ለማስፈታት መብቃታቸውን ነው፡፡ የሽማግሌቹ ቡድን መሪ የሆኑት ፐ/ር ኤፍሬም ይስሀቅ በእለቱ «የአገር ችግር ለመፍታት ፍቱን መድሀኒቱ ባእዳን ሳይሆኑ የሀገር ተወላጆች መሆናቸውን ያመንን እኛ የአገር ሽማግሌዎች ከማንኛውም ፖለቲካዊ፤ ኃይማኖታዊ፤ የወገናዊነት አድልዎና ጫና ነፃ በሆነ መንፈስ በራስ ተነሳሽነትና በጋለ የሀገር ፍቅር ስሜት ብቻ ተነሳስተን ምርጫ 97ትን ተከትሎ በአገራችን በተፈጠረው አለመግባባት ምክንያት ችግሩ ሠላማዊ እልባት እንዲያገኝ በአገራዊ ወግ መሠረት መፍትሔ ለማፈላለግ 18 ወራት ያህል ጥረት ስናደርግ ቆይተናል» በማለት የተናገሩት የጉዳዩን ምንነትና የአፈፃፀሙን እንዴትነት በግልጽ ያመላከተ ነው፡፡ በተለይም በአገራዊ ወግ መሠረት በማለት የተናገሩት የይቅርታ አጠያየቁን ባህርይ ገላጭ ነው፡፡

ከአንድ ዓመት ተኩል በላይ ጉዳዩ በተለያየ መልክ በቃልም በጽሁፍም ሲገለጽ ከቆየ በኋላ፤ ዛሬ አጀንዳ ተደርጎ የቀረበበት ምክንያት ሌላ ሣይሆን የአንድነት ፓርቲ ጠንካራ አማራጭ እየሆነ መምጣቱ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ የፍትህ ሚኒስቴር በሁለቱ መግለጫዎች የተለያዩና ለጉዳዩ አግባብነት የሌላቸው አንቀፆችን መጥቀሱ በቂ ማረጋገጫ ሲሆን አጠቃላይ ድርጊቱ ህግንና ህጋዊነትን ያልተከተለ የህግ ብቻ ሳይሆን የሰብአዊ መብት ጥሰትም የተፈፀመበት እና ግልጽ የሆነ ሠላማዊ ትግል የሚያደናቅፍ ተግባር መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በመሆኑም፡-

1ኛ/ በወ/ት ብርቱካን ሚደቅሣ ላይ የተፈፀመው ከሕግ ውጭ የሆነ ድርጊት ያስቆጣን መሆናችንን እየገለጽን ዛሬም ሆነ ነገ የፓርቲያችን ሊቀመንበር መሆናቸውን እናረጋግጣለን፡፡

2ኛ/ ሴቶች በፖለቲካ ተሳትፎና በውሳኔ ሰጪነት የጎላ ሚና እንዲኖራቸው ማድረግ የዓለም አቀፉ አስተሳሰብ የሚያበረታታውና የሚደግፈው ሆኖ በአገራችን አንድ እንስት በፖለቲካ መሪነት ብቅ ስትል ያለ አግባብ ማጨናገፍ በኢትዮጵያችን ልንገነባ የምንሻውን ዴሞክራሲያዊ ሂደት የሚያጨናግፍ ድርጊት ስለሆነ የአንድነት ሊቀመንበር ወ/ት ብርቱካን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ከእሥር እንዲፈቱ እንጠይቃለን፡፡

3ኛ/ በኢትዮጵያችን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እውን ሆኖ ለማየት የሚሹ በሀገር ውስጥም ሆነ በመላው አለም የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ለእውነትና ለህግ የበላይነት መከበር በጽናት ቆመው ለእስር የበቁትን የአንድነት ፓርቲ ሊቀመንበር መታሠርን አስመልክቶ የተቃውሞ ድምፃቸውን እንዲያሰሙ ጥሪ እናቀርባለን፡፡

4ኛ/ የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) ሊቀ መንበሯን በማሰር የተፈፀመው ተግባር አጠቃላይ የዴሞክራሲዊ ስርዓት ግንባታ ሂደት ላይ የተቃጣ አደጋ መሆኑን በመገንዘብ ኢትዮጵያዊያን የፖለቲካ ፓርቲዎች ሁሉ በሕጋዊ መንገድ የበኩላችሁን ድርሻ ትወጡ ዘንድ ጥሪ እናቀርባለን፡፡

5ኛ/ ለህግ የበላይነት መከበር ለሰብአዊ መብት መረጋገጥና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እውን መሆን የቆሙ መንግሥታትና ድርጅቶች ሁሉ የፓርቲያችንን ሊቀመንበር ለማስፈታት በምናደርገው ትግል ከጎናችን እንዲቆሙ ጥሪ እናቀርባለን፡፡

6ኛ/ የሕግ መጣስ ከማንም በላይ ቅድሚያ ሊመለከታቸው የሚገባው የህግ ባለሙያዎች የተፈፀመውን ድርጊት ከህጉ ጋር እያነፃፀሩ እውነቱን በመግለጽ ሙያዊ ግዴታቸውን እንዲወጡ እንጠይቃለን፡፡

7ኛ/ የ18 ወራት የሽምግልና ጥረታቸው ለፍሬ በመብቃቱ ሐምሌ 13/1999 ዓ.ም በኢትዮጵያ ቴሌቭዥን ደስታቸውን ሲገልፁ የተመለከትናቸውና በቅርቡም በአሜሪካን ሐገር በዚሁ ተግባራቸው ለሽልማት የበቁ የሀገር ሽማግሌዎች ታሳሪዎቹ በተፈቱበት ጊዜ ቃል በገቡት መሠረት የእርቅ ሂደቱን እውነተኛ ገጽታ የመናገሪያው ወቅት አሁን ነውና የእርቅ ሂደቱን እውነተኛ ገጽታና የተደረሰበትን ስምምነት ለሕዝብ በይፋ እንዲገልፁ በአጽንኦት እንጠይቃለን፡፡

8ኛ/ በህግ ብቻ ሣይሆን በሀገራችን ባህልም ሴቶችና አረጋዊያን ይከበራሉ፡፡ የፓርቲያችንን ሊቀመንበር ለመያዝ የተሠማሩት የፀጥታ ኃይሎች ግን ከ10 ያላነሱ ከመሆናቸው አልፎ ወ/ት ብርቱካንን አንገላተዋቸዋል፡፡ የፓርቲያችንን የብሔራዊ ምክር ቤት አባል የሆኑትን አንጋፋውን ምሁር ፕ/ር መስፍን ወ/ማሪያምን በሰደፍ መተዋቸዋል፤ በወ/ት ብርቱካን ሾፌር በአቶ አብዱራህማን አህመድ ላይም ከባድ ድብደባ ተፈጽሞበታል፡፡

ይህን ህገወጥና ከኢትዮጵያዊ ባህልና  ሰብአዊ ባህርይ ውጭ የሆነ ተግባር የፈፀሙት ተለይተው ለህግ እንዲቀርቡ እንጠይቃለን፡፡

9ኛ/ በጥበቃ ስር ያሉና በፍርድ የታሰሩ ሰዎችን መብት የሚደነግገው የመጠየቅና የመጎብኘት ህገ መንግስታዊ መብት ተጥሶ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን ጠያቂ እንዳይጎበኛቸው ተደርጓል፡፡ ይህ የህግ ጥሰት በአስቸኳይ እንዲታረም እየጠየቅን የኢትዮጵያ እና አለም ዓቀፍ ቀይ መስቀል ማህበራትና የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች ታሳሪዋን በመጎብኘት የሚገኝ በትን ሁኔታ ለህዝብ ይፋ እንዲደርጉ ጥሪ እናቀርባለን፡፡

10ኛ/ ኢትዮጵያ የሁላችንም የጋራ ሀገር ናትና ሐገራዊ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታው ሊሣካ የሚችለው በሁሉም ዜጎች የድርሻ አስተዋጽኦ እንጅ በአንድ ፓርቲ አውቅላችኋለሁ ባይነት ሊሆን ስለማይችል የፖለቲካ ምህዳሩ ሁሉንም ወገን  በነፃነትና በእኩልነት ማንቀሳቀስ የሚያስችል እንዲሆን  የማድረግ ኃላፊነቱን መንግሥት እንዲወጣ አበክረን እንጠይቃለን፡፡

11ኛ/ ፖለቲካዊ ፍላጎትን በህግ ሽፋን ለመፈፀም ሲባል የሚደረጉ ህገ ወጥ ተግባራት እንዲቆሙና ማንም ሰው ከህግ በላይ  አይደለም የሚለው የህግ መርህ በማናቸውም ደረጃ ላይ በሚገኙ መንግሥታዊ አካላትና ባለሥልጣናት ላይ ተግባራዊ እንዲሆን እንጠይቃለን፡፡

12/ ሊቀመንበራችንን ለማስፈታት የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው የተጠናከረ ሕጋዊ ዲፕሎማሲያዊና  ፖለቲካዊ ትግል እንዲያደርግ  ምክር ቤቱ መመሪያ ሰጥቷል፡፡

**በመጨረሻም:-**

አንድነት በሠላማዊ ትግል አምኖና ለዚህም ተደራጅቶ ትግል ሲጀምር በፕሮግራሙ ላሠፈራቸው ዓላማዎች ተፈፃሚነት በጽናት ሊታገልና በኢትዮጵያ አስተማማኝ የዴሞክራሲ መሠረት ለመጣል የበኩሉን ለማበርከት ጠንካራ ተፎካካሪ ለመሆን እንጅ የአጃቢነት ሚና ለመጫወት እንዳልሆነ አስረግጠን ለመግለጽ እንወዳለን፡፡

የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት)
ብሔራዊ ምክር ቤት
ታህሣሥ 25 ቀን 2001 ዓ.ም
አዲስ አበባ